**አዋጅ ቁጥር ___/2016**

# የአረንጓዴ አሻራ እና የተጎሳቆለ መሬት ማገገሚያ ልዩ ፈንድን ለማቋቋምና አስተዳደሩን ለመወሰን የወጣ አዋጅ

የተጎሳቆለ መሬት መልሶ እንዲያገግም በማድረግ፣ የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ ደኖችን በመጠበቅና በመንከባከብ ለአገራችን ዘላቂነት ያለው ኢኮኖሚያዊ፤ ማህበራዊና የሥነ ምህዳር ጥቅም እንዲሰጥ ማድረግ በማስፈለጉ፣

ለአረንጓዴ አሻራ ስራዎች ቋሚና ተቋማዊ ሥርዓት ያለው የፋይናንስ አቅም እንዲኖር ማስቻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በዘላቂነት የአየር ንብረት ለውጥን የሚቋቋም እና ከአየር ንብረት ብክለት የፀዳ ኢኮኖሚ ለመገንባት የተያዘውን አገራዊ ራዕይ እንዲሳካ አስተዋፅኦ ማድረግ በማስፈለጉ፤

እነዚህን ዓላማዎች ተግባራዊ ለማድረግ የተቀናጀ ቋሚና ዘላቂነት ያለው የሀገር ውስጥ የፋይናንስ ምንጭ በመመደብና በማሰባሰብ ሁሉም ክልሎች ፍትሃዊ በሆነ መንገድ ተጠቃሚ የሚሆኑበትን አሰራር መቀየስ ተገቢና ለዚኅም የአረንጓዴ አሻራ እና የተጎሳቆለ መሬት ማገገሚያ ልዩ ፈንድ ማቋቋም አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 55(1) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ “የአረንጓዴ አሻራ እና የተጎሳቆለ መሬት ማገገሚያ ልዩ ፈንድ ማቋቋሚያና አስተዳደር አዋጅ ቁጥር ___/2016 ተብሎ” ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. ትርጓሜ

የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፣

1/ “ክልል” ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 47 በተደነገገው መሰረት ማንኛውም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባና የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደርን ይጨምራል፡፡

2/ “የሚመለከተው የስራ ክፍል” ማለት በገንዘብ ሚኒስቴር የተባበሩት መንግስታት ተቋማት፣ ለአየር ንብረት የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚ ፋሲሊቲ እና የአህጉራዊ ኢኮኖሚ ትብብር የስራ ክፍል ነው፡፡

3/ “አረንጓዴ አሻራ” ከ2011 ዓ.ም ጀምሮ በመካሄድ ላይ የሚገኝ ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ ያላቸው ከአካባቢ ጋር ተስማሚ የሆኑ ቋሚ ዕጽዋትን በህብረተሰብ ተሳትፎ የማልማት ፕሮግራም ነው፡፡

4/ “የተጎሳቆለ መሬት” ማለት የስርዓተ-ምህዳር አገልግሎቱ የቀነሰና ምርታማነቱን ያጣ በመሆኑ የማገገም ስራዎች ሊሰሩበት የሚገባ መሬት ነው፡፡

5/ “የተጎሳቆለ መሬት ማገገም” ማለት የተጎሳቆለ መሬትን ለደን ልማት እና ለጥምር ደን ግብርና እንዲውል ማድረግ ነው፡፡

6/ “ቀመር” ማለት በፌዴራል መንግስት ለክልሎች ከተመደበው የልዩ ፈንዱ በጀት ላይ የያንዳንዱን ክልል ድርሻ ለመወሰን የሚያገለግል ስሌት ነው፡፡

7/ “ተጠቃሚ አካላት” ማለት በልዩ ፈንዱ የሚደገፉ ፕሮጀክቶችን የሚተገብሩ የፌዴራል መንግስት ተቋማት እና ክልሎች ሲሆኑ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 8 ንኡስ አንቀጽ 2 መሠረት አብይ ኮሚቴው ለዚህ አላማ የሚያወጣውን መመዘኛ የሚያሟሉ ሌሎች አካላትን ይጨምራል

8/ “የልማት አጋሮች” ማለት ለልዩ ፈንዱ የፋይናንስ፣ የቴክኒክና የዓይነት ድጋፍ የሚሰጡ አለም አቀፍ ተቋማት፣ መንግስታት፣ ግብረሰናይ ድርጅቶችና ፋውንዴሽኖች ናቸው፡፡

## ክፍል ሁለት

## ስለ ልዩ ፈንዱ መቋቋም

### 3. መቋቋም

1/ የአረንጓዴ አሻራ እና የተጎሳቆለ መሬት ማገገሚያ ልዩ ፈንድ /ከዚህ በኋላ “ልዩ ፈንዱ” እየተባለ የሚጠራ/ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፡፡

2/ ልዩ ፈንዱ ቋሚ የፋይናንስ ምንጭ ሆኖ ለዚህ አዋጅ አላማ ማስፈጸሚያ ይውላል፡፡

### 4. የልዩ ፈንዱ አላማዎች

ልዩ ፈንዱ የሚከተሉት ውስን ዓላማዎች ይኖሩታል፡፡

1/ የተጎሳቆለ መሬት በተፈጥሮና በመልሶ ማልማት መርህ በመታገዝ እንዲያገግም በማድረግ የደን ልማት እና የደን መልሶ ማልማትን መደገፍ፣

2/ በአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብር እና በዜጎች ተሳትፎ የተተከሉ ችግኞች እና ያገገሙ መሬቶች ውጤታማ እንዲሆኑና ዘለቄታ እንዲኖራቸው መደገፍ፣

3/ የደን ልማትና የደን ጥበቃ እንዲሁም ተዛማጅ የስርዓተ-ምህዳር አገልግሎቶችን በማሻሻል ለዜጎች በተለይም ለወጣቶችና ሴቶች ዘላቂነት ያለው የስራና የመተዳደሪያ ስራ ዕድል መፍጠር፣

4/ ከአካባቢ ጋር ተስማሚ የሆኑ ቋሚ ዕጽዋትን መሰረት በማድረግ የወንዞች፣ የግድቦችና ሌሎች የውሃ አካላት ዳርቻዎችን መልሶ ማልማት፣

5/ የከተማ ማስዋብና አረንጓዴ ልማት ስራዎችን መደገፍ፣

6/ ሀገራችን በዓለም አቀፍ ደረጃ የደን ዘርፍን ማዕከል ባደረገ መልኩ ለማሳካት ያቀደቻቸውን ግቦች፣ በተለይም የካርቦን ልቀት ቅነሳ ግብ እንዲሳካ አስተዋጽኦ ማድረግ፣

7/ ከልማት አጋሮች ለደን ልማትና ጥበቃ የሚገኝ ድጋፍ እንዲጨምር ማድረግ፤

8/ በልዩ ፈንዱ ከለማ ደን በአለም አቀፍ የካርቦን ግብይት ሀገራችን ተጠቃሚ እንድትሆን ማስቻል፣

9/ ከአየር ንብረት ለውጥ ቅነሳ እና ስርፄት ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን ምርምሮችና ፈጠራዎች መደገፍና አቅም መገንባት

## 5. <u>የልዩ ፈንዱ የፋይናንስ ምንጮች</u>

ልዩ ፈንዱ ከሚከተሉት የፋይናንስ ምንጮች የተውጣጣ ይሆናል።

1/ የፌደራል መንግሥት ከሚመድበው በጀት፤

2/ ከልማት አጋሮች፣ ከሲቪክ ማህበረሰብ እና ከግል ዘርፍ ከሚገኝ ድጋፍ፤

## 6. <u>የፈንዱ ተሰብሳቢ ገንዘብ መጠንና ገንዘቡን ገቢ ስለማድረግ</u>

1/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት ለልዩ ፈንዱ የሚመደበው ገንዘብ የፌዴራል መንግስት በየዓመቱ ከሀገር ውስጥ ገቢ ምንጭ ከሚመድበው ዓመታዊ በጀት ውስጥ ከ0.5 እስከ 1.0 በመቶ ያህል ይሆናል። የፌዴራል መንግሥት ለልዩ ፈንዱ የሚመድበው አመታዊ በጀት የፌዴራል መንግስት ዓመታዊ በጀት አካል ሆኖ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ይጸድቃል።

2/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 5 ንኡስ አንቀጽ 1 መሠረት ፌዴራል መንግሥት ለልዩ ፈንዱ ከሚመድበው በጀት የሚሰበሰበው ገንዘብ ለልዩ ፈንዱ በተከፈተው የባንክ ሂሳብ በየሦስት ወሩ በገንዘብ ሚኒስቴር ተቀማጭ ይሆናል፡፡

3/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት ከልማት አጋሮች፣ ከሲቪክ ማህበራት እና ከግሉ ዘርፍ ለልዩ ፈንዱ የሚደረገው ድጋፍ የሚተዳደርበት አኳኋን የገንዘብ ሚኒስቴር በሚያወጣው መመሪያና የአሰራር ሥርዓት ይወሰናል፡፡

## 7. <u>የልዩ ፈንዱ የሀብት ክፍፍልና አለቃቀቅ</u>

1/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የፌደራል መንግሥት ለልዩ ፈንዱ የሚመድበው ዓመታዊ በጀት የገንዘብ ሚኒስቴር በሚያወጣው መስፈርት መሠረት ለፌደራል መንግሥት እና ለክልሎች ይደለደላል፡፡

2/ የገንዘብ ሚኒስቴር በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት ለክልሎች ከሚደለደለው በጀት ላይ የእያንዳንዱን ክልል ድርሻ ለመወሰን የሚያገለግለውን ቀመር አዘጋጅቶ እንዲጸድቅ ለፌዴሬሽን ምክር ቤት ያቀርባል፡፡ ሆኖም ለመሸጋገሪያ የፌዴሬሽን ምክር ቤት ያፀደቀው ጠቅላላ የበጀት ድጋፍ ቀመር በጥቅም ላይ ሊውል ይችላል፡፡

3/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ቢኖርም የፌደራል መንግሥት ለልዩ ፈንዱ ከሚመድበው በጀት ላይ የአዲስ አበባ እና የድሬ ዳዋ ከተማ አስተዳደርን ድርሻ ለመወሰን የሚያገለግለው ቀመር በገንዘብ ሚኒስቴር ተዘጋጅቶ ከሁለቱ የከተማ አስተዳደሮች ጋር በሚደረግ ምክክር በሚደረስበት መግባባት መሰረት ይወሰናል፡፡

4/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ከተደለደለው ዓመታዊ የሀብት ድርሻ ላይ በየሶስት ወሩ ወደ ተጠቃሚ አካላት ገንዘብ ሊተላለፍ የሚችለው፦

ሀ) የስራ አፈፃፀምን መሠረት በማድረግ

ለ) ክልሎች ተጓዳኝ በጀት ሲመድቡና በክልሉ ለሚተገበሩ ፕሮጀክቶች ፈሰስ ሲያደርጉ ይሆናል፡፡

ሐ) ክልሎች ከዚህ በላይ በተራ ፊደል ‘ለ’ መሰረት የሚመድቡት ዝቅተኛ ተጓዳኝ በጀት ተፈጻሚ የሚሆነው በተጓዳኝ በጀቱ መጠን ላይ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 10 በተዘረዘሩት አካላት መካከል በሚደረግ ምክክር የጋራ ስምምነት ሲደረስና በየክልሉና በከተማ አስተዳደሩ ምክር ቤቶች ሲጸድቅ ይሆናል፡፡

5/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 በተደነገገው መሰረት እስከ በጀት ዓመቱ መጨረሻ ድረስ ሳይተላለፍ የቀረ ገንዘብ በሚቀጥለው በጀት ዓመት ለልዩ ፈንዱ ከሚመደበው በጀት ጋር ተደምሮ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት ይደለደላል፡፡

## 8. የልዩ ፈንዱ ተጠቃሚ አካላት

1/ በልዩ ፈንዱ የሚደገፉ ፕሮጀክቶችን የሚያስፈጽሙ የፌዴራል መንግሥት አካላት እና ክልሎች ከልዩ ፈንዱ በቀጥታ ተጠቃሚ ይሆናሉ፡፡

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ከተደነገገው በተጨማሪ አብይ ኮሚቴው በሚያወጣቸው መመዘኛዎች መሠረት ሌሎች አካላት ከልዩ ፈንዱ ተጠቃሚ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

## 9. ስለ ልዩ ፈንዱ ሂሳብ

1/ ተጠቃሚ አካላት በልዩ ፈንዱ ድጋፍ የሚተገብሯቸውን ፕሮጀክቶች የሂሳብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በተመለከተ ትክክለኛና የተሟላ የሂሳብ መዛግብት መያዝ አለባቸው፡፡

2/ ተጠቃሚ አካላት የበጀት አመቱ በተጠናቀቀ በአንድ ወር ውስጥ ከፌዴራል መንግስት የተላለፈላቸውን የልዩ ፈንዱን ገንዘብ አጠቃቀም የሚያሳይ የሂሳብ ሪፖርት አዘጋጅተው ለገንዘብ ሚኒስቴር ያቀርባሉ፡፡

3/ የገንዘብ ሚኒስቴር በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 2 መሠረት ከተጠቃሚ አካላት የሚቀበለውን የሂሳብ ሪፖርት በማጠቃለል የልዩ ፈንዱን ሂሳብ ዘግቶ የበጀት አመቱ በተጠናቀቀ በሶስት ወራት ውስጥ በፌደራል ዋና ኦዲተር ወይም የፌደራል ዋና ኦዲተር በሚወክለው ኦዲተር እንዲመረመር ያደርጋል፡፡

4/ የፌደራል መንግሥት ለልዩ ፈንዱ የሚመድበው የበጀት አጠቃቀም የኦዲት ምርመራ ውጤት የበጀት ዓመቱ ባለቀ በስድስት ወራት ውስጥ ለአብይ ኮሚቴው ይቀርባል፡፡

## ክፍል ሦስት

## ስለ ልዩ ፈንዱ አስተዳደር

## 10. የልዩ ፈንዱ አስፈፃሚ አካላት

የፈንዱ አስፈፃሚ አካላት የገንዘብ ሚኒስቴር፣ የግብርና ሚኒስቴር፣ የፕላንና ልማት ሚኒስቴር፣ የኢትዮጵያ ደን ልማት እንዲሁም የክልሎች የገንዘብ ቢሮዎች ናቸው፡፡

## 11. አብይ ኮሚቴ

1/ ልዩ ፈንዱ አጠቃቀሙና አተገባበሩን በበላይነት የሚቆጣጠር አብይ ኮሚቴ ይኖረዋል፡፡

2/ የአብይ ኮሚቴው አባላት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 10 የተዘረዘሩት የልዩ ፈንዱ አስፈፃሚ አካላት የበላይ ኃላፊዎች ይሆናሉ፡፡

3/ የገንዘብ ሚኒስትርና የግብርና ሚኒስትር እንደቅደም ተከተላቸው የአብይ ኮሚቴው ሰብሳቢና ምክትል ሰብሳቢ ይሆናሉ፡፡

4/ የሚመለከተው የስራ ክፍል የፈንዱን አስተዳደራዊ ስራዎች ያከናውናል እንዲሁም የአብይ ኮሚቴው ፀሐፊ በመሆን ያገለግላል፡፡

## 12. <u>የአብይ ኮሚቴው ስልጣንና ተግባር</u>

1/ አብይ ኮሚቴው የልዩ ፈንዱን አጠቃቀምና አተገባበር ይቆጣጠራል፤

2/ የልዩ ፈንዱን የፕሮግራም ማዕቀፍ፣ እስትራቴጂና መመሪያዎች ያጸድቃል፤

3/ በልዩ ፈንዱ የሚደገፉ ፕሮጀክቶችን ያጸድቃል፤

4/ የልዩ ፈንዱን አጠቃላይ አፈጻጸም ይገመግማል፤

5/ የልዩ ፈንዱን የኦዲት ሪፖርት ውጤት ያዳምጣል፤ በሪፖርቱ መሰረት ተገቢው እርምጃ መወሰዱን ያረጋግጣል፤

6/ መቋረጥና መሰረዝ በሚገባቸው ፕሮጀክቶች ላይ ይወስናል፤

7/ መመዘኛዎችን በማውጣት ተጨማሪ አካላት ከልዩ ፈንዱ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ያደርጋል፡፡

## 13. <u>የአብይ ኮሚቴው ስብሰባዎች</u>

1/ የአብይ ኮሚቴው ስብሰባ በዓመት አንድ ጊዜ ይካሄዳል፣ ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ በሰብሳቢው ሲጠራ በማንኛውም ጊዜ አስቸኳይ ስብሰባ ሊያደርግ ይችላል፡፡

2/ በማንኛውም የአብይ ኮሚቴው ስብሰባ ላይ ከግማሽ በላይ አባላት ከተገኙ ምልዐተ ጉባዔ ይሆናል፡፡

3/ የአብይ ኮሚቴው ውሳኔ የሚተላለፈው በስብሰባው ከተገኙት አባላት በአብላጫው ድምጽ ሲደገፍ ነው፡፡ ሆኖም ድምጽ ዕኩል በዕኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል፡፡

4/ የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው አብይ ኮሚቴው የራሱን የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡

14. <u>የገንዘብ ሚኒስቴር ሥልጣንና ተግባር</u>

1/ ልዩ ፈንዱን ያስተዳድራል፣

2/ በፌዴራል መንግስት ለልዩ ፈንዱ በየዓመቱ የሚመደበውን በጀት መጠን ያቀርባል፣ የፌዴራል መንግስት ዓመታዊ በጀት አካል ሆኖ እንዲጸድቅ ያደርጋል፤

3/ የፌዴራል መንግሥት ለልዩ ፈንዱ ከሚመድበው በጀት ላይ የክልሎች ድርሻ ለያንዳንዱ ክልል የሚከፋፈልበትን ቀመር አዘጋጅቶ ለፌዴሬሽን ምክር ቤት ያቀርባል፣ ሲጸድቅም በስራ ላይ ያውላል፤

4/ የፌደራል መንግስት ተጠቃሚ አካላትና ክልሎች የፌዴራል መንግሥት ለልዩ ፈንዱ ከሚመድበው በጀት ላይ የሚያገኙትን ጥቅል ድርሻ የሚወሰንበትን መስፈርት ያዘጋጃል፣ በመስፈርቱ መሰረት የበጀት ክፍፍሉን ያዘጋጃል፣

5/ በፌዴሬሽን ምክር ቤት ቀመር መሰረት የሚወሰነውን የእያንዳንዱን ክልል ድርሻ ለየክልሉ ያሳውቃል፣

6/ ልዩ ፈንዱ ለአምስት ዓመት የሚመራበት ሀገራዊ የፕሮግራም ማዕቀፍ በየአምስት ዓመቱ ተዘጋጅቶ ለአብይ ኮሚቴው እንዲቀርብ ያደርጋል።

7/ የልዩ ፈንዱን አስተዳደር፣ ፕሮግራም/ፕሮጀክት አስተዳደር፣ የፋይናንስ አስተዳደርና ቁጥጥርን በተመለከተ መመሪያ ያወጣል፣ የአሰራር ስርዓት ይዘረጋል፣ ከነዚህም ጋር በተያያዘ የአቅም ግንባታ ስራዎችን ያካሂዳል።`

8/ በተጠቃሚ አካላት የተዘጋጁ የፕሮጀክት ጽንሰ ሀሳቦችና የፕሮጀክት ሰነዶች በሚመለከተው አካል ተገምግመው ሲቀርቡ በአብይ ኮሚቴው እንዲጸድቁ የውሳኔ ሀሳብ ያቀርባል፣ የግምገማ ውጤቱን ያሳውቃል።

9/ ተጠቃሚ አካላት ለጸደቁ ፕሮጀክቶች አመታዊ የስራ ዕቅድና የጥሬ ገንዘብ ፍላጎት እንዲያዘጋጁ ያደርጋል፣ በጀት ይለቃል።

10/ በልዩ ፈንዱ የሚተገበሩ ፕሮጀክቶችን አፈጻጸም ይከታተላል፣ ይገመግማል፣ አጠቃላይ ሪፖርት ያዘጋጃል።

11/ ከልማት አጋሮች፣ ከሲቪክ ማህበራት እና ከግል ዘርፍ ለልዩ ፈንዱ ድጋፍ ያሰባስባል፤

12/ ከአለም አቀፍ የካርቦን ንግድ ተጠቃሚ መሆን እንዲቻል በልዩ ፈንዱ የሚደገፉ ፕሮጀክቶችን መሰረት በማድረግ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ሁኔታዎችን ያመቻቻል፣ ስምምነት ይፈጽማል፡፡

13/ በዚህ አዋጅ አንቀፅ 9 (3) መሠረት ልዩ ፈንዱን ኦዲት ያስደርጋል፡፡

14/ የልዩ ፈንዱን አብይ ኮሚቴ በሰብሳቢነት ይመራል፡፡

## 15. <u>የግብርና ሚኒስቴር ሥልጣንና ተግባር</u>

1/ የልዩ ፈንዱን አብይ ኮሚቴ በምክትል ሰብሳቢነት ይመራል፡፡

2/ የልዩ ፈንዱን የቴክኒክ እስታንዳርድና አሰራር መመሪያ ያወጣል፣ ትግበራውን ይከታተላል፣ የአቅም ግንባታ ስራዎች ይሰራል፡፡

3/ ልዩ ፈንዱ ለአምስት ዓመት የሚመራበትን ሀገራዊ የፕሮግራም ማዕቀፍ በየአምስት ዓመቱ ከኢትዮጵያ ደን ልማት ጋር በመሆን የሚመለከታቸውን በማሳተፍ ያዘጋጃል፡፡

4/ በዚህ አዋጅ ለኢትዮጵያ የደን ልማት የተሰጡ ተግባራትንና ሀላፊነቶችን ይከታተላል፣ በበላይነት ይቆጣጠራል፣ ድጋፍ ያደርጋል፡፡

## 16. <u>የፕላንና ልማት ሚኒስቴር ሥልጣንና ተግባር</u>

1/ የልዩ ፈንዱን የፕሮግራም ማዕቀፍ ዕቅድ ይገመግማል፣ የግምገማውን ውጤት ያሳውቃል፡፡

2/ የልዩ ፈንዱን የፕሮግራም ማዕቀፍ አፈጻጸም የመካከለኛና ማጠናቀቂያ ግምገማ ያከናውናል፡፡

## 17. <u>የኢትዮጵያ የደን ልማት ስልጣንና ተግባር</u>

1/ የልዩ ፈንዱ የፕሮጀክት ጽንሰ ሀሳብና የፕሮጀክት ሰነድ እንዲቀርብ ያደርጋል፣ ከሚመለከታቸው ተቋማት ጋር በመሆን ይገመግማል፣ የውሳኔ ሀሳብ ለገንዘብ ሚኒስቴር ያቀርባል፤

2/ በልዩ ፈንዱ ሊለሙ የሚችሉ ቦታዎች የሚለዩበትና የሚተከሉ የችግኝ ዝርያዎች የሚመረጡበትን አሰራር ያዘጋጃል፣ ክልሎችን ይደግፋል፡፡

3/ በልዩ ፈንዱ የሚተገበሩ ፕሮጀክቶች ከአለም አቀፍ የካርቦን ገበያ ተጠቃሚ መሆን እንዲችሉ አስፈላጊውን የመነሻ እና የልኬት፣ የሪፖርት እና የማረጋገጥ ስራዎች እንዲጠናቀቁ ያደርጋል፤

4/ በልዩ ፈንዱ ድጋፍ የሚተገበሩ ፕሮጀክቶች ያስገኙትን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ፣ የካርቦን ልቀት ቅነሳ እና ስርዓተ-ምህዳራዊ ጠቀሜታ ሪፖርት ያዘጋጃል፤

5/ በዚህ አዋጅ የተሰጡትን ተግባራትና ሀላፊነቶች ለመወጣት የሚያስችሉ የአቅም ግንባታ ስራዎችን ያከናውናል፡፡

## 18. <u>ተጠቃሚ የፌደራል መንግሥት ተቋማት</u>

በልዩ ፈንዱ ተጠቃሚ የሆኑ የፌደራል መንግሥት ተቋማት የሚተገበሯቸውን ፕሮጀክቶች ፅንሰ ሀሳብና የፕሮጀክት ሰነድ አዘጋጅተው ያቀርባሉ፣ ሲፀድቅም ይተገበራሉ፣ አፈፃፀሙን ይከታተላሉ፣ ሪፖርት ያቀርባሉ፡፡

## 19. <u>በልዩ ፈንዱ የሚደገፉ ፕሮጀክቶችን በሚመለከት እና የክልሎች ተግባርና ኃላፊነት</u>

ክልሎች

1/ ለልዩ ፈንዱ ተጓዳኝ በጀት በየዓመቱ ይመድባሉ፤

2/ ለልዩ ፈንዱ የሚለሙ ቦታዎችን ይመርጣሉ፤ ያዘጋጃሉ፤ ህጋዊ የይዞታ ማረጋገጫ ይሰጣሉ፤

3/ በልዩ ፈንዱ በሚተገበሩ ፕሮጀክቶች ተጠቃሚ የሚሆኑ ማህበረሰቦችን ያደራጃሉ፣ ህጋዊ ዕውቅና ይሰጣሉ፤

4/ በልዩ ፈንዱ የሚተገበሩ ፕሮጀክቶች ፅንሰ ሀሳብና የፕሮጀክት ሰነድ አዘጋጅተው ያቀርባሉ፣ ሲጸድቅም ይተገበራሉ፣ አፈጻጸማቸውን ይከታተላሉ፣ ሪፖርት ያቀርባሉ፡፡

## 20. <u>የልዩ ፈንዱ አስተዳደር በጀት</u>

ልዩ ፈንዱን ለማስተዳደር የሚያስፈልገው በጀት በየዓመቱ ከልዩ ፈንዱ የሚመደብ ይሆናል፡፡

## ክፍል አራት

## <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

21. **<u>ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ሕጎች</u>**

ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማናቸውም ሕግ እና ልማዳዊ አሰራር በዚህ አዋጅ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

22. **<u>ደንብ እና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን</u>**

1/ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ ለማስፈፀም የሚያስችል ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡

2/ የገንዘብ ሚኒስቴር ይህን አዋጅ እና በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) መሠረት የወጡ ደንቦችን ለማስፈፀም የሚያስችል መመሪያ ያወጣል፡፡

**<u>23. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

*አዲስ አበባ ______ ቀን 2016 ዓ.ም*

*ሳህለወርቅ ዘውዴ*
*የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ*
*ፕሬዘደንት*